## ለመጭው የአምስተርዳም ስብሰባ ማስታወሻ

የፖሪሱን ጉባኤ ጥንስስ እንደገና ለማንቀሳቀስ ሙከራዎች ሲደረጉ መቆየታቸው የሚታወስ ነው:: ነገር ግን በኛው በራሳችን የያዝ ለቀቅ አሰራርና በየድርጅቶቻችን የዓላማና ተግባር ትኩረቶች መሰበጣጠር የተነሳ እስካሁን ይህንን ሃሳብ እውን ለማድረግ ተስኖን ቆይቷል::

በዚህ ላይ ደግሞ በአጠቃላይ የትግሉ መፍዘዝና ሰፍኖ የነበረው አፖቲ ይህንን የጋራ ትግል ጉዳይ ቸላ ብለነው ቆይተናል:: አሁን ደግሞ በኢህአዴግና በሻቢያ መሃከል በተነሳው ግጭት ምክንያት በያለበት የትግል ወኔ እየተቀሰቀሰ እናያለን:: የጋራ ኢኒሽቲቮች እየተባሉ የጋራ መግለጫዎች፣ የትግል አግጣጫ ሃሳቦች እንደ አሸን የሚፈሉበት አስደናቂና አጣዳፊ ወቅት ውስጥ እየገባን ነው:: ቀደም ሲል የነበረው አጠቃላይ መፋዘዝ የትም ያላደረሰንን ያህል የአሁኑ በየአግጣጫው መራወጥም መልክና ትክክለኛ አግጣጫ ካልያዘ ውዥንብሩ የሚረዳው ለኢህአዴግና ለሌሎች አክራሪዎች እንጂ ለሃገራችንና ለዲሞክራሲያዊው ትግላችን የሚፈይደው ጉዳይ አይኖርም::

በያለበት በመፍላት ላይ ያሉትን ኢኒሽቲቮስ አንድ ዲሞክራሲያዊ አግጣጫ ለመስጠትና ለማስተባበር የሃገራችን ዲሞክራቶች በእጥፍ ድርብ ታታሪነትና ጥራት መንቀሳቀስ የሚገደዱበት ወቅት ውስጥ ነን:: ለእንደዚህ ዓይነቱም እንቅስቃሴ መነሻ ሊሆን የሚችለው የፖሪሱ ጥንስስ እንደሆነ ለብዙዎቻችን ግልጽ ይመስለናል::

ከዚህ በመነሳት ለውይይታችን እንዲረዳ አንደኛ በመፍላት ላይ ካሉት ኢኒሽቲቮች ሁሉ ለምን የፖሪሱ ጥንስስ ይመረጣል? የሚለውን ጥያቄ ሁለተኛ ደግሞ የት ለመድረስ በየት እንጀምር ለሚለው ጥያቄ የመልስ ሃሳቦች ልሰንዝር::

### አንደኛ/ ለምን እንደገና ወደፖሪስ?

የፖሪሱ ጥንስስ የሰላምና እርቅ ጉባኤ የማዘጋጀት ሂደት ብቻ አልነበረም::በኢትዮጵያ ህዝቦች ፊት ለተደቀኑት ዋና ዋና የፖለቲካ ችግሮች የተለያዩ ድርጅቶች የጋራ አቋም ይዘው የተንቀሳቀሱበት ሂደት ነበር:: እነዚህ የጋራና ዲሞክራሲያዊ አቋሞች በራሱ በፖሪሱ መግለጫ፣ ከዚያም ይበልጥ ደግሞ በአስተባባሪው ኮሚቴ በጸደቀ ሰነዶች የተንጸባረቀ አቋሞች ነበሩ:: በተለይ ለአዲስ አበባው ጉባኤ የተሰናዳው ሰነድ በዲሞክራሲ፣ በብሄር ጥያቄና በኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ፣ በነጻ ምርጫና በዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ጥያቄ፣ በህዝቦች መሃከል መተማመን እንዲኖር እርምጃዎች መወሰድ እናዳለባቸውና የተቃዋሚ ኃይሎች የትግል አንድነት ጉዳይ... እነዚህን ሁሉ አስመልክቶ ዲሞክራሲያዊ የጋራ አቋም ለመያዝ ረድቷል:: እነዚህ አቋሞች ዛሬ ጊዜ ያለፈባቸውና ያረጁ የሚባሉ አይደሉም:: እንዲያውም ሰሞኑን ከምናያቸው አስደናቂ ክስተቶች አንጻር ከተነሳን የፖሪሱን ስምምነቶች ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አጥብቀን እንድንገፋባቸው የምንገደድበት ሁኔታ አለ ባይ ነን:: ለምን?

ባለፉት አራት ዓመታት በፖሪሱ የጋራ አቋማችን በጋራ መቀጠል ባለመቻላችን፣ ዲሞክራሲያዊ ትግሉም ጠንካራና የተባበረ አመራር በማጣቱ የህዝቡን የትግል አንድነት ኢሉታ ሌሎች 'አጠራጣሪ' አካባቢዎች ሊጠቀሙበት ሲሞክሩና የተሳሳተ አግጣጫ ሊያስይዙት ሲሞክሩ አይተናል:: እነዚህ የጋራ ትግል ጥሪዎችና ጥረቶች በፖሪሱ ጠንሳሾች የተወሰዱትን ትክክለኛና ዲሞክራሲያዊ አቋሞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከጥያቄ ውስጥ እያስገቡ የተደረጉ ጥሪዎች ናቸው:: እነዚህ አካባቢዎች በዚህ መልክ ሲያደርጉ ከርመው በሰሞኑ ግጭት ሳቢያ ይፋ እየወጡ ናቸው:: በኢትዮጵያ አንድነት ስም የብሄሮችን የመብት ጥያቄ ተገቢነ

ት ለመከድ ዳርዳር ማለት፣ አቶ መለስ ዜናዊን "ባድመን ካስመለሱ በኋላ በነካ እጅዎ ምጽዋንም እንዳይረሱ አደራ" ብሎ በይፋ ጥሪ ማድረግ፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም በሶሻሊዝም ስም በመነገዱና ይህ ነው የማይባል ግፍ በመፈጸሙ ሌላው ቀርቶ 'ማህበራዊ ፍትህ' ሲባል አንስማ እንደተባለው ሁሉ አቶ መለስ ዜናዊ 'በብሄሮች የራስን እድል በራስ መወሰን' ስም ሁኔታውን ስላጨማለቁት እኩልነትም ሆነ የህዝቦች መብት ጥያቄ ሲነሳ "አድርስናል" ለማለት የሚቃጣቸው ኃይሎች እንደ አሸን መፍላት፣ ይህ ደግሞ የግድ የሚያግዘውና የሚያጉለብተው የጠባብ ብሄረተኛነት አደጋ .... እነዚህ ክስተቶች ሁሉ የሚያመለክቱት አንድ ነገር ነው:: የፓሪሱ አቋማችንን ከመቸውም ይበልጥ አድሰን በአንድ ላይ መራመድና ውሽንብሩን ለማጥራት ካልሞከርን ኢትዮጵያ ወደ ባሰ ጥፋትና ትርምስ የምትጓዝበት አደጋ አለ::

ሁለተኛ የዲሞክራሲ ትግሉም ጥያቄ አለ:: አሁን በመንፈስ ላይ ባለው አየር ታግዘው የወያኔ መሪዎች ልክ በደርግ ጊዜ እንዳየነው 'አሁን የሃገር አንድነትን የመሰለ ቁም ነገር ስለተያዘ ዲሞክራሲ ብሎ መለፍለፍ አይቻልም' የሚል ክርክር በያለበት እያሰሙ ናቸው:: ወደድንም ጠላንም ይህ አስተሳሰብ የማይናቅ ተቀባይነት አለው:: ድፍን አገር ተፍቷቸው በሃይልና በአመጽ ሲገዙ የቆዩ ኃይሎች አገዛዛቸውን በዚህ ግርግር ለማጠናከር መሞከራቸው አይቀርም:: ከሁለት ወር በፊት አቶ መለስ ዜናዊን እንዴት አርገን እንዋጋ በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ተከፋፍሎ ሲለፈለፈስና ሲተራመስ የቆየው ኃይል አሁን ደግሞ 'ለጊዜውም ቢሆን ለቀቅ እናድርግ ወይስ አፋጠን እንያዛቸው' በሚለው ጥያቄ ላይ እየተከፈለ እና የዋለን:: ይህም በመሆኑ ያለው ውሽንብር ሊጠራ የሚችለው ግልጽ በሆነ ሁኔታ በዲሞክራሲ፣ በነጻ ምርጫ፣ በሰው ልጅ መብት ጥያቄዎች የፓሪሱን የጋራ አቋም አድሶ በዚያ በጋራ መቆምና ኃይል መሰብሰብ ሲቻል ብቻ ነው::

ሁለተኛ/ የት ለመድረስ ከየት እንጀምር?

የፓሪሱን ኢኒሼቲቭ እንደገና እናንቀሳቅስ ሲባል ካሁኑ የት ለመድረስ በሚለው ጥያቄ ላይ ተወያይተን ግልጽ የጋራ አቋም ከሌለን የትም መድረስ አንችልም:: የጋራ ትግላችን ዓላማ ኢትዮጵያ የህዝቦቿን ሁሉ እኩልነትና አንድነት በሚያንጸባርቅ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት እንድትተዳደር የሚያስችላት ነጻ ምርጫ እንዲካሄድ ለዲሞክራሲ አመቺ የሆነ የኃይል ሚዛን ለመፍጠር የሚደረግ ትግል መሆን አለበት:: ይህንን ለማድረግ በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ አቋም በጋራ መያዝ ይኖርብናል:: ለዚህ ሂደት እንዲረዳ የሚከተለውን አቅጣጫና ቀደም ተከተል ይዞ መራመድ ስለሚያስፈልግ እንደሚከተለው ፕሮሲድ ማድረግ ይቻላል፣

1ኛ/ የአምስተርዳሙ ስብሰባ የመጀመሪያ ተግባር ባጭር ባጭሩም ቢሆን በአስተባባሪው ኮሚቴ ተወስደው የነበሩትን ዋና ዋና የፖለቲካ አቋሞች ማደስ ይኖርበታል:: ይህንን ስናደርግ እንደ ዛሬ አራት ዓመቱ ከዳር እስከዳር ድጋፍ እናገኛለን ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው:: ከአንዳንድ አካባቢዎች 'ዛሬ ሁኔታው ተቀይሯል' በሚል ሰበብ ተቃውሞ እንደሚመጣ መጠበቅና ለመታገል መዘጋጀት ያስፈልጋል::

2ኛ/ በዚያው በአስተባባሪው ኮሚቴ ሰነድ ላይ በተለይ ስለ ምርጫና ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት የተባለውን እንደገና በይፋ ማጽደቅ:: ከዚሁም በማያያዝ በዚህ ጉዳይ ላይ ለነጻ ምርጫ ጥሪ ከማድረግ አልፎ በመሄድ ነጻ ምርጫና ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ሲባል ምን እንደሆኑ 'ለአዲስ ዲሞክራሲያዊ ጅማሮ' በተባለው ሰነድ ላይ በግልጽ የተቀመጡ ነገሮች አሉ:: በሁለቱም አንጻር የተባለው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ያጸደቃቸው መስፈርቶች ስለሆኑ እነሱን መቀበል ብዙ ችግር የሚፈጥር አይመስለኝም::

የሚቀየሩ ነገሮችም ካሉ ብዙ አይሆኑም:: ለማንኛውም ከእንግዲህ ዝም ብሎ ነጻ ምርጫና ዲሞክራሲያዊ ሀገ መንግሥት እያሉ በደፈናው መጓዝ ስለማይቻል በዚህ ሰነድ ላይ ተወያይተን የሚቀየር ነገር አለ ካልን ቀይረን በዚህ ጥያቄ ላይ አንድ የጋራ ሰነድ መያዝ የትግሉ መጀመሪያ ምእራፍ ይመስለናል:: ይህንን ካደረግን የጋራ ሰነዳችን በሰፊው እንዲሰራጭ ማድረግ ያስፈልጋል::

3ኛ/ በዚህ የጋራ ሰነድ አማካኝነት በሃገር ውስጥ ካሉት አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትና ሌሎች ዋና ዋና ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ተደራድሮ የውስጡም የውጪም የሚስማማበት አንድ የጋራ አቋም/ሰነድ መያዝ

4ኛ/ በዚህ ሰነድ አማካኝነት ኢህአዴግን በተለይ የመጭው የ1992 ዓ.ም.ን ምርጫ ዝግጅት አስመልክቶ ውይይት በመጥራት ቻሌንጅ ማድረግ

5ኛ/ ኢህአዴግ መጣ አለመጣ ዘሮ ዘሮ በዚህ በጋራ በያዝነው አማራጭ ዙሪያ ህዝቡን ማደራጀትና ማታገል ዋና ጥያቄ በመሆኑ ልክ ከፓሪስ በኋላ እንደተደረገውና "የሰላምና እርቅ ጉባኤ ድጋፍ ኮሚቴያች" እንደተቋቋሙት አይነት አሁንም ለዚህ ኢኒሽቲቭ በውስጥም በውጭም የተደራጀ ድጋፍ የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት::

ይህ እንግዲስ ስለመጭው ስብሰባችን ዓላማና አካሄድ የቀረበ የሃሳብ ረቂቅ ነው:: ያለው ጊዜ አጭር ስለሆነ አስፈላጊ ከሆነ ሌሎችም ሃሳቦችና የአጀንዳ ነጥቦች መወያየት ይቻላል:: ስብሰባውም ላይ ስለዓላማውም ሆነ ስለ ሂደቱ በቅድሚያ ተወያይተን የሁለት ቀናቱ ስብሰባችን ፍሬያማ እንዲሆን የሁላችንንም የጋራ ጥረት ይጠይቃል::

ነገደ

18/06/98

001-202-2690991

owneR - 0044171-8352205